## ስያሜያችን---ኢወክንድ

## ልሳናችን -- ነቅንቅ

**ልዩ መግለጫ** ታህሣሥ 2002

## ወጣት ሰማዕቶቻችን ሲታሰቡ

የኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ድርጅት ስለሆንነን ብቻ አይደለም ወክንድን መጣሪያችን ያደረግነው።

የሕዝባችንን ነፃነትና የሀገራችንን ክብር አስመላሽ ክንድ መሆናችንን ለመግለፀ ፈልገን እንጂ።

ላይ ታቹ በወጣቶቻችን ደም የረሰረሰውን አካይስት የወያኔ ሥርዓት ካልተነቀነቀነ አይነቀልም

ለማለት ፈልገን ነው ልሳናችንንም ነቅንቅ ብለን የሰየምነው።

እንደ ኮንጎዎች ደም በምሥራቅ ከተሞች

ሁሌ እንደሚፈሰው

የሲዳማን መሬት ሻኪሶን ከተማ የኛዎቹ አራሰው።

የወጡና የገቡ፤ ያለፉና የሚያልፉት አምባገነን የኢትዮጵያ ሥርዓቶች የአነድበታቸወ የመክፈቻ ኳኳታ ዴሞ ክራሲን ያደርጉና፤ በምላሳቸው ዴሞክራሲን ያንቆረቁሩና ደም የለመደው የፈሪ ጣታቸው ደግሞ ቃታ ይስብ ና የሕዝብ ልጆችን ደም ያንቆረቁራል። በተለይ በዓይናችን እያየነው፤

የሥርዓቱን ክርፋት እየታጠንነው ያለው ቅጥረኛ ወያኔ ፍረሀቱ ልኬታ የለውምና ከሕዝብ ሆ

የሚል የተባበረ ድምፅ በሰማ ቁጥር አካላቱ መረስረሱን ለመሸፋፈን፤የፍርሀት ቆፈኑን ለመደበቅ የተኩስ ግርግ ር ባልታጠቁ ወጣቶች ላይ በመልቀቅ ሊጀግን ይሞክራል። ያለ ማሰቢያ ተፈጥሯልና፤ ለሀገር በማሻያስቡ ዉ ሮቶች በቅንዓት ይቃጠልና፤ የድሀ ልጆችን በጥይት አረር ያቃጥላል።

ዛሬ እቡዩ ዜናዊ " ኢትዮጵያ" የሚል የለበጣ ቅላፄ ከመጀመሩ በፊት የዛሬ 17 ዓመት የኮሌጅ

ለጋዎች ኢትዮጵያ አትከፈልም በማለታቸው ብቻ ነበር በወያኔ ጉጅሌዎች በወርሃ ታህሳስ በሳንጃየታረዱት። በ91 ዓ.ም ዴሞክራሲ ለሕዝብ ያሉትን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የዚሁ ቀፎ ስርዓት ታጣቂዎች ተኩስ ከፍተው የ 6 ኪሎን አደባባይ በታህሣሥ የገና ዋዜማ ደም ያጠጡት። በ91፣ በ92፣በ93 እያልን በወያኔ የተመተሩትን ወጣቶች እንዘክር ብንል የ95፣የ96፣የ97ቱን እያልን

በወያኔ ሰለባ የሆኑትን አፍላ ችግኝ ወጣቶቻችንን መዘርዘር ብንጀምር ማለቂያ የለውምና ቤት

ይቁጠረው ብለን ባናልፍም በልባችን ማህተም የሆኑ ሰማዕቶቻችንን ፈለግ ተከታዮች መሆናችንና፣ ወክንድም ነንና ፈርጥመን ስርዓቱን ለማድቀቅ መዘጋጀታችንን በሰማዕቶቻችን ደም ቃል

እንገባለን።

የዚህ መግለጫ ጭብጡ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት በአላሙዲና በወዲ ዜናዊ ጭምር ኩባንያ

ኢትዮጵያ አትመዘበርም ባሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ዉሮት የሻኪሶ ትንታጎች የረሸነውን የወያኔን

አራጅ ቡድንክፉኛ ለመኮነን ይሆናል።

የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት፣-

የሻኪሶ ወጣቶች ግድያ ትንሳዔ ለኢትዮጵያ ነውና፣

በሀገር ፍቅር የነደደውን ፣ በወያኔ ጥይት የሞቀውን አካለታቸውን ለመንፈሳችን ብርታት፣

ለትግላችን ነዳጅነት ብንጠቀምበት እንደማያዝኑብን በኩራት እንገልፃለን።

የአካላችን ክፋይ የሆኑት የሻኪሶ የ 2ኛ ደረጃ ወጣት ተማሪዎች ትግልና መስዋዕትነት ዘራፊው አገዛዝና ሽሪኮቹ ከሚዘርፉት የአዶላ ወርቅ ባለይ ዕንቁ ስለሆነ ምን ጊዜም ከልባችን አይጠፋም።በዚህም አጋጣሚ የምናዝነው በክብር ለተሰዉት ወጣቶቻችን ሳይሆን ቀኑ እየጨለመ ለመጣበትየወያኔ አገዛዝና ስርዓት ይሆናል። ለ ኢትዮጵያ የደቡብ በረኛ ሆነው ለህብቱ ዘብ ቆመው ለተሰዉወጣቶች ወላጆቻቸውና ወዳጆቻቸው ሁሉ ኢወክንድ መፅናናትን እየተመኘ ገዳዮቹን ወያኔዎችንና ወርቅ ዘራፊዎቹን ከማውገዝ በላይ ዘለል የምን የነፃነት ክንዶች መሆናችንን አስረግጠን

በኢትዮጵያ ወጣቶች ስም እንገልፃለን። የሻኪሶ ወጣቶች ቀንዲል በጠቅላላ በምድረ ኢትዮጵያ

ይቀጣጠል ዘንድ ኢወክንድ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ፣ በአጠቃላይም ለኢትዮጵያ ወጣቶች በሞላ

ነፃነታችንን፤ ክብራችንን፤ ሕዝባችንን፤ድንግል መሬታችንን ከአዲስ ቅኝ ገዢ እንዲያስመልስ ጥሪእናደርጋለን ::

የኢወክንድ መግለጫ የሚደመደመው ለወያኔ ሥርዓት ስንኝ በመቋጠር ነው፤

እናንተም ግደሉ እኛም እንሞታለን

እናንት ግን ትቢያ እኛ እንነሳለን!

ኢትዮጵያ በወጣቶቿ መስዋዕትነት ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!

ኢወክንድ

ታህሣሥ 2002